# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

## OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፬
አዲስ አበባ ግንቦት ፳፭ ቀን ፪ሺህ፲ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No. 24
Addis Ababa, 2nd June , 2018


**ማውጫ**


**ደንብ ቁጥር ፻/፪ሺ፲**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተሻሻለ የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ደንብ ገጽ ፩ሺ፫፻፺፮**


**CONTENTS**


**REGULATION NO 100/2018**

**Addis Ababa City Government Revised Integrated Solid Waste Management Regulations Page 1396**


## ደንብ ቁጥር ፻/፪ሺ፲
## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተሻሻለ የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ደንብ

በከተማዋ የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ስርዓትን በመተግበር በዘርፉ የሚታየውን የመልካም አስተዳደር ችግር በመቅረፍ የከተማዋ ጽዳት አሁን ካለበት ዝቅተኛ ደረጃ ወደ ተሻለ እርከን ለማሸጋገር በማስፈለጉ፡፡

## REGULATION NO.100/2018
## ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT REVISED INTEGRATED SOLID WASTE MANAGEMENT REGULATION

**WHEREAS,** it is found necessary to enhance the sanitation of the city to a better level from its current situation and alleviating the good governance problems exhibited in the sector by implementing an integrated solid waste management system in the city;


ያንዱ ዋጋ
Unit Price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ደንብ ቁጥር ፲፫/፲፱፻፺፮ የደረቅ ቆሻሻ፣ የፍሳሽ ቆሻሻና የውበትና ፓርክ ተግባራት ተቀላቅለው ለአንድ ኤጀንሲ የተሰተጠ ሲሆን ነገር ግን በአሁን ወቅት እነዚህን ተግባራት የተለያዩ ተቋማት የሚያስተዳድሩት ተግባር በመሆኑ ይህን ደንብ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፳፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ረ) እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፬ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፹፬ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ <<የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተሻሻለ የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ደንብ ቁጥር ፻/፪ሺ፲>> ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**WHEREAS,** it is found necessary to amend the Solid Waste Handling and Disposal Regulation No 13/2004 as the Solid Waste, Sewrage and Beautification and Parks administration activities were given to a single agency in a mixed manner; but currently these activities given to various institutions;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with sub-article 1 (f) of Article 23 of the Addis Ababa City Government Revised Charter Proclamation No 361/2003 (as amended) and Article 84 of the Addis Ababa City Government Executive and Municipal Service Organs Re-establishment Proclamation No 35/2012 (as amended), the Cabinet of the Addis Ababa City Government has issued this regulation as follows.

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This regulation may be cited as the "Addis Ababa City Government Revised Integrated Solid Waste Management Regulation No. 100/2018."

## ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. <<**ከተማ**>> ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፡፡

፪. <<**????**>> ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ኤጀንሲ ነው፡፡

፫. <<**ክፍለ ከተማ**>> ማለት የከተማው ሁለተኛ የሆነ የአስተዳደር እርከን ነው፡፡

፬. <<**ወረዳ**> >ማለት የከተማው ሶስተኛ ደረጃ የአስተዳዳር እርከን የሆነ የክፍለ ከተማ አካል ነው፡፡

፭. <<**ደንብ ማስከበር**>> ማለት የደንብ ጥሰትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የደንብ ማስከበር አገልግሎትን ለማስፈፀም የተቋቋመ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት ነው፡፡

፮. <<**ደስት ቢን**>> ማለት ኤጀንሲው በሚያወጣው ስታንዳርድ መሰረት በመንገድ ዳር፤ መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች/ተቋማት፤ የንግድ ማዕከላት ለጥቃቅን ደረቅ ቆሻሻ ጊዜያዊ ማስቀመጫነት ሚያገለግል እቃ ነው፡፡

## 2. Definition

In this regulation, unless the context requires otherwise:

1. **"City"** means the Addis Ababa City;
2. **"Agency"** means Solid Waste Management Agency of Addis Ababa City Government.
3. **"Sub-City"** means the second administrative stratum of the city;
4. **"Woreda"** means the third administrative stratum of the city which is a unit of the sub-city;
5. **"Code Enforcement"** means the code enforcement office of the Addis Ababa city government which was established to prevent and control code violations and execute code enforcement services;
6. **"Dustbin"** means a container used for putting temporarily small solid wastes and placed at road sides and at close quarters of governmental and non-governmental organizations as per the standard of the agency;

፯. <<**ደረቅ ቆሻሻ**>> ማለት ከመኖሪያ ቤት፣ ከንግድ፣ ከኢንዱስትሪ፣ ከተለያዩ ተቋማት፣ ከጋራዥ፣ ከመንገድ ጽዳት፣ ከግብርና፣ በእንስሳትና በጠቅላላው ከህብረተሰቡ ስራዎች ምክንያት የሚፈጠር ጥቅም የማይሰጥ ወይም የማይፈለግ ተብሎ የሚጣል ጠጣር ወይም ከፊል ጠጣር የሆነ ቁስ ነው፡፡

፰. <<**ጥቃቅን ደረቅ ቆሻሻ**>> ማለት በየቦታው በግልፅ የሚታዩና በሰዎች እንቅስቃሴ ምክንያት ተጠቃሚዎች የሚጥሏቸው የሲጋራ ቁርጥራጭ፣ የሶፍት ወረቀት፣ ፌስታል፣ የጫት ገለባ፣ የፍራፍሬ ተረፈ-ምርቶች፣ የትራንስፖርት ቲኬት፣ የሞባይል ካርዶችን፣ የማስቲካና ከረሜላ ሽፋኖች፣ ወዘተ የመሳሰሉትን የሚያጠቃልል ነው፡፡

፱. <<**የኤሌክትሮኒክስ ነክ ቆሻሻዎች**>> ማለት እንደገና አገልግሎት ሊሰጡ ወይም ላይሰጡ የሚችሉ ኮምፒዩተሮች፣ ፎቶ ኮፒ ማሽኖች፣ ማንኛውም የስልክ ቀፎ፣ ቴሌቪዥኖች፣ የማቀዝቀዣ መሳሪያዎች፣ ወዘተ እና የእነዚህ ዕቃዎች የውስጥና የውጭ ስብርባሪና የወላለቁ አካላት ማለት ነው፡፡

፲. <<**???? ??? ???**>> ማለት የሚፈነዱ፣ በቀላሉ በእሳት የሚቀጣጠሉ፣ መርዛማ ነገሮች፣ ራዲዮአክቲቭ ቁሶች፣ ልዩ ልዩ ኬሚካሎች፣ የደም ንኪኪ ያላቸው ሆነው ከኢንዱስትሪ፣ ከማምረቻ ተቋማት፣

7. **“Solid Waste”** means any solid or semi-solid material generated from houses, business institutions, Industries, various organizations, garage, street cleaning, construction, agriculture, animals and generally from the activities of the society and dumped as it is useless or unwanted.

8. **“Tiny Solid Waste”** means solid wastes which are visible everywhere and dumped by users as a result of their movement and which includes cigarette tips, soft papers, plastic bags, transport ticket, mobile cards, covers of chewing gum and candies and so forth;

9. **“Electronics Related Wastes”** means re-usable or worn –out computers, photocopiers, any telephones, televisions, refrigerators and so forth; and damaged and ruined internal and external bodies of the thereof;

10. “**Hazardous Solid Waste”** mean explosives, flammables, toxic substances, radioactive materials, various chemicals, and those wastes generated from industries, manufacturing institutions,

ከጤና ተቋማት ወይም ከቤተ ሙከራ የሚወጡና በሰው፣ በእንስሳ፣ በእጽዋትና በአካባቢ ላይ ጉዳት የሚያደርስ ማንኛውም ቆሻሻ ነው፡፡

health institutions or laboratories which have contact with blood that causes harm to human beings, animals, plants and the environment;

፲፩. <<**የመንገድ ጽዳት**>> ማለት የአንድን መንገድ ግራና ቀኝ ጠርዞች፣ የእግረኛ መንገድና አካፋይ መንገድ ማጽዳት፣ ጥቃቅን ቆሻሻዎች የሚጣሉበት የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ዕቃዎችን ማራገፍ፣ መንገድ በሚያልፍባቸው ድልድዮች አካባቢ በሕገ-ወጥ ተግባር የሚጣለውን ደረቅ ቆሻሻ መከላከልና ማጽዳትን ያካትታል፡፡

11. **“Road cleansing”** means activities that include cleaning of road sides, pedestrian path and median strips; preventing and cleaning of solid wastes dumped on bridges where a road passes through as a result of illegal action;

፲፪. <<**ደረቅ ቆሻሻ ከምንጩ መለየት**>> ማለት ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያና ስታንዳርድ መሰረት ደረቅ ቆሻሻን የሚያመነጨው አካል በግቢው ውስጥ ደረቅ ቆሻሻን እንደ ተፈጥሮአዊ ባህሪው ለይቶ ለየብቻ ማከማቸት ነው፡፡

12. “Separation of Solid Waste at the Source” means the separation and accumulation of solid wastes as to their nature by the source of the thereof in a particular place as per the directive and standard to be issued by the agency;

፲፫. <<**??? ??? ? ????? ? ???**>> ማለት ኤጀንሲው በሚያወጣው ስታንዳረርድ መሰረት ደረቅ ቆሻሻን ከምንጩ በዓይነት ለይቶ ወደ ጊዜያዊ ማቆያ ማዕከላት፣ ኡደት ማዕከላት፣ ማቃጠያና ማስወገጃ ቦታ ማጓጓዝ ነው፡፡

13. **“Collection and Transportation of Solid Waste”** means the transportation of solid wastes to temporary storage centers, recycling centers, incineration and disposal area by separating the solid wastes from the source as to their nature as per the standard to be issued by agency;

፲፬. <<**መልሶ መጠቀም**>> ማለት ከደረቅ ቆሻሻ ውስጥ ጠቃሚ ዕቃዎችን በማውጣት በቀጥታ ወይም የተወሰነ ለውጥ አድርጎ ለተመሳሳይ ወይም ለተለየ አገልግሎት መጠቀም ማለት ነው፡፡

፲፭. <<**መልሶ ኡደት ማድረግ**>> ማለት ከደረቅ ቆሻሻ ውስጥ ጠቃሚ ዕቃዎችን በማውጣት በጥሬ ዕቃነት በመጠቀም ከመጀመሪያው ዕቃ ጋር የሚመሳሰል ወይም የማይመሳሰል ጠቃሚ ዕቃ ማምረት ነው፡፡

፲፮. <<????? ???>> ማለት ደረቅ ቆሻሻ ከምንጩ በተሽከርካሪዎች እየተሰበሰበ ለጊዜው የሚቆይበት፣ እንደሁኔታውም በዓይነት የሚለይበትና ጥቅም የማይሰጠው፣ ወደ ማስወገጃ ቦታ በተሽከርካሪዎች ለማጓጓዝ የሚያስችል የመቀባበያ ጣቢያ ነው፡፡

፲፯. <<**ቆሻሻን በከፍተኛ ሙቀት ማቃጠል**>> ማለት ከሸክላ ጡብ፣ ከወፍራም ብረት፣ ከድንጋይ ወይም በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተሰራ መሳሪያ በመጠቀም ሊቃጠሉ የሚችሉ ደረቅ ቆሻሻዎችን በከፍተኛ ሙቀት (በኦክሲጅን ወይም ያለ ኦክሲጅን) ሁከትና ብክለት በማይፈጥር ሁኔታ በማቃጠል ለጤና ጎጂ ወዳልሆነ ዝቃጭ ወይም አመድ መለወጥ ነው፡፡

14. **“Reuse”** means the extraction of usable materials from solid wastes and use them for a similar or different purpose by directly or slight modifications;

15. **“Recycling”** means the production of an important material, which is similar to or different from the original, by extracting usable materials from solid wastes and use it as a raw material;

16. **“Transfer Station”** means a temporary gathering station where solid wastes are collected from the sources, separated as to their nature where necessary and to transport useless wastes to a disposal site using garbage trucks;

17. **“Incineration”** means the burning of wastes in a chamber made of clay, standardized metal, stone or advanced technologies using high energy (with or without oxygen) in a way no to create disorder or pollution and changing the thereof into sludge or ashes which are not hazardous to health;

፲፰. <<? ???? ?? >> ማለት ምንም ጥቅም የማይሰጠውን ደረቅ ቆሻሻ በመሬት ላይ ወይም በመሬት ውስጥ ለጤናና ለአካባቢ ጠንቅ በማይሆንበት መንገድ የሚደፋበት፣ የሚከማችበት፣ የሚቀበርበት ወይም የሚወገድበት ስፍራ ነው፡፡

፲፱. <<???? ??? ???? ?????? ?? ????>> ማለት ደረቅ ቆሻሻን ከምንጩ የመሰብሰብ፣ የማጓጓዝ፣ የማስወገድና የመንገድ ጽዳትና አገልግሎት የሚሰጡ በግል፣ በማህበር፣ በሽርክና፣ በዩኒዬን፣ ወዘተ የሚሰሩና የደረቅ ቆሻሻ የጽዳት አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች ናቸው፡፡

፳. <<**የመልሶ መጠቀምና ኡደት ድርጅት**>> ማለት በግል፣ በማህበር፣ በሽርክና፣ በዩኒዬን፣ ወዘተ የሚሰሩና ደረቅ ቆሻሻን ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት የሚያውሉ ድርጅቶች ወይም ፋብሪካዎች ናቸው፡፡

፳፩. <<?? >> ማለት በተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

፳፪. <<???? ? ???? ???>> ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተደደር የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽሕፈት ቤት ደንብ ቁጥር ፶፬/፪ሺ፭ ነው፡፡

18. “**Landfill”** means a dumping, accumulation, burying or removal site for non-usable dry wastes on the ground or under the soil in a way not harmful to health or the environment;

19. **“Solid Waste Cleaning Service Providing Organization”** means organizations involved in the collection of dry wastes from the source, its transportation, removal of such and street cleaning; and which provides the solid waste cleaning service individually, in association, forming share holding, union or etc.;

20. **“Reusing or Recycling Organization”** means organizations that reuse or recycle dry wastes and works privately, in association, forming share holding, union and so forth;

21. **“Person”** means any natural person or juridical person;

22. **“Code Enforcement Regulation”** means the Addis Ababa city government office of the code enforcement service regulation No. 54/2013.

፫. **የፆታ አገላለፅ**

በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

3. **Gender Reference**

Provisions of this regulation set out in the masculine gender shall also apply to the feminine gender.

፬. **የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

4. **Application Scope**

This regulation shall be applicable within the Addis Ababa City Government.

## ክፍል ሁለት
## ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ በዓይነት መለየት፣ አጓጓዝ፣ መልሶ መጠቀም፣ ኡደትና ማስወገድ

## Part Two
## Handling, Separation, Transportation, Reusing, Recycling and Disposal of Solid Wastes

፭. **የደረቅ ቆሻሻ አያያዝን በተመለከተ የተከለከሉ ድርጊቶች**

፩. ማንኛውን መኖሪያ ቤት ወይም ድርጅት ያመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ በሰው፣ በእንስሳት፣ በአካባቢና በሌሎች ሰዎች ድርጅት፣ ጤናና የከተማዋን ጽዳት ገጽታ ሊያበላሽ በሚችል መልኩ መያዝ ወይም ማከማቸት የተከለከለ ነው፡፡

፪. ማንኛውም የጽዳት አገልግሎት ሰጭ ድርጅት ደረቅ ቆሻሻ ከደንበኛው ሲረከብ አካባቢው ላይ ማዝረክረክና ማንጠባጠብ የተከለከለ ነው፡፡

5. **Prohibited Actions Concerning handling of Solid Wastes**

1. Carelessly handling or collecting of solid wastes generated from houses or organizations in a way that such causes harm to the wellbeing of humans, animals, the environment, other organization and damage the image of the city's sanitation;
2. Carelessly collect and drop solid wastes while receiving such from customers by any cleaning service providing organization.

## ፮. <u>የደረቅ ቆሻሻ አያያዝን በተመለከተ የተጣሉ ግዴታዎች</u>

፩. ከመኖሪያ ቤት ወይም ከድርጅት የሚመነጭ ደረቅ ቆሻሻ ተሰብስቦ እስከ ሚወገድ ድረስ ቆሻሻውን ያመነጨው አካል ኤጀንሲው ባወጣው ስታንዳርድ መሰረት በዓይነት ለይቶ የማጠራቀም ግዴታ አለበት፡፡

፪. ከመኖሪያ ቤት ወይም ከድርጅት የሚመነጭ ደረቅ ቆሻሻ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሰረት ኤጀንሲው ባወጣው የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ስታንዳርድ መሰረት በማጠራቀም ለጽዳት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች የማስረከብ ግዴታ አለበት፡፡

፫. ከመኖሪያ ቤት ወይም ከድርጅት የሚመነጭ ደረቅ ቆሻሻ በቆይታ ምክንያት የጤና ችግር ወይም የአካባቢ ብክለት በማያስከትል ሁኔታ መያዝና ማጠራቀም ይገባዋል፡፡

፬. ማንኛውም የመኖሪያ ቤት አከራይ በግቢው ውስጥ ያለው ተከራይ ደረቅ ቆሻሻን በአግባቡ እንዲይዝና እንዲለይ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

## ፯. <u>ደረቅ ቆሻሻ መሰብሰብና ማጓጓዝን በተመለከተ የተጣሉ ግዴታዎች</u>

## 6. <u>Obligations Concerning Management of Solid Wastes</u>

1. A body which generates solid wastes from houses or organization shall have the obligation to separate and collect such as to their nature according to the standard set by the agency until it is collected and disposed.

2. The body that generates solid wastes shall have the obligation to deliver such to the cleaning service provision organization according to sub-article one of this article.

3. A solid waste generated from houses or organization should be collected and kept in a way not to create health problem or environmental pollution through time.

4. Any individual that rents a house shall have the obligation to cause his renter to separate and collect solid wastes in this compound.

## 7. <u>Obligations Concerning Collection and Transportation of Solid Wastes</u>

፩. ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ ከመኖሪ ቤትና ከድርጅት የሚሰበስብ የጽዳት ድርጅት ከኤጀንሲው እውቅናና ውል ሊኖረው ይገባል፡፡

፪. ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻን ከመኖሪ ቤት ወይም ከድርጅት የሚሰበስብ የጽዳት አገልግሎት ሰጭ ድርጅት ኤጀንሲው ባወጣው ወይም በሚያወጣው የተሽከርካሪ ስታንዳርድ መሰረት ደረቅ ቆሻሻውን መሰብሰብና ማጓጓዝ ይገባዋል፡፡

፫. ማንኛውም የጽዳት አገልግሎት ሰጭ ድርጅት ኤጀንሲው ባወጣው ስታንዳርድ መሰረት ለደንበኞቹ በስታንዳርዱ መሰረት አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

፬. ማንኛውም የጽዳት አገልግሎት ሰጭ ድርጅት ደረቅ ቆሻሻ በተሽከርካሪ ወደ ቅብብሎሽ ጣቢያ፤ መልሶ መጠቀምና ኡደት ማዕከላት ወይም ማስወገጃ ቦታ ሲያጓጉዝ በጉዞ ላይ ቆሻሻ በንፋስ እንዳይበተን በሽፍን ተሽከርካሪ ወይም ሙሉ በሙሉ በመረብ የመሸፈን ግዴታ አለበት፡፡

፭. ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ እስከ ማስወገጃ ቦታ እንዲያጓጉዝ ፈቃድ የተሰጠው የጽዳት ሽርክና ማህበር ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የማጓጓዝ ግዴታ አለበት፡፡

1. Any cleaning organization that collects solid waste from houses and organization should be recognized and have a contract with the agency.

2. Any cleaning service providing organization that collects solid wastes from houses and organizations should collect and transport such as per the vehicle standard issued or to be issued by the agency

3. Any cleaning service providing organization shall have the obligation to provide its service to its customers as per the standard issued by the agency.

4. Any Cleaning service providing organizations shall have the obligation to use garbage trucks or cover the solid waste with a net while transporting the thereof using vehicles to transfer stations, reusing and recycling centers or to landfills to prevent spreading of solid waste due to wind.

5. Any cleansing share holding association that have a licence to transport solid upto the disposal site shall have the obligation to transport as per the directive to be issued by the agency.

## ፰. ደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀም፣ ኡደትና ማስወገድ በተመለከተ የተከለከሉ ድርጊቶችና የተጣለ ግዴታ

፩. የተለያዩ እቃዎች ተጠቅልሎባቸው ወደ ሀገር ውስጥ ከሚገቡት ውጭ ውፍረታቸው 0.03 ሚ.ሜና በታች የሆኑ የእቃ መያዣ ፕላስቲክ ፌስታል በከተማው ውስጥ ማምረት፣ መሸጥ፡ ለእቃ መያዣነት መጠቀም፣ ከቦታ ቦታ ማዘዋወር፣ ወደ ከተማው ማስገባት፣ በመጋዘንና በንግድ መደብር ማስቀመጥና መሸጥ፣ በምርት ማሸጊያነት መጠቀም፣ በታሸጉ ምርቶች ላይ ለማስታወቂያነት መለጠፍ የተከለከለ ነው፡፡

፪. ኤጀንሲው በሚያወጣው ስታንዳርድ መሰረት ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት የሚውሉ ደረቅ ቆሻሻዎችን ወደ ማስወገጃ ቦታ ማጓጓዝና ማስወገድ የተከለከለ ነው፡፡

፫. ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት የሚውሉ ደረቅ ቆሻሻዎችን ህጋዊ ፈቃድ ወይም ህጋዊ ውክልና ሳይኖረው ከየትኛውም ቦታ መሰብሰብም ይሁን ማከማቸት የተከለከለ ነው፡፡

## 8. Prohibited Actions and Obligations Concerning Reusing, Recycling and Disposal of Solid Wastes

1. It is prohibited to produce plastic bags of 0.03 mm thickness and below except those which enters to the country in wrapping up various materials, sell it, use it for handling of materials, move it from place to place, enter into the city, store and sell it in warehouses and business stores, wrapping up products and attach it on products for advertisement purpose.

2. It is prohibited to transport and dispose solid wastes which could be used for the reusing and recycling purpose as per the standard set by the agency.

3. It is prohibited to collect solid wastes which could be used for reusing or recycling purpose from anywhere or accumulate the thereof without having a legal permit or legal representation.

፬. ማንኛውም ሰው በደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ውስጥ ከኤጀንሲው ህጋዊ ፈቃድ ሳይኖረው ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት የሚውሉ ደረቅ ቆሻሻዎችን መልቀም፣ ማከማቸትና መጫን የተከለከለ ነው፡፡

፭. ማንኛውም የመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት የሚውሉ ደረቅ ቆሻሻዎችን ሰብስቦ አገልግሎት ላይ የሚያውል ድርጅት ከኤጀንሲው ፈቃድ ወይም የድጋፍ ደብዳቤ ሊኖረው ይገባል፡፡

## ክፍል ሶስት

## ደረቅ ቆሻሻ ስለመጣል

### ፱. የተከለከሉ ድርጊቶች፡-

፩. ማንኛውንም ደረቅ ቆሻሻ በተሽከርካሪ መንገድ፣ በባቡር ሀዲድ፣ አውቶብስ መነኻሪያዎችና ፌርማታዎች፣ በእግረኛ መንገድ፣ በአደባባይ፣ በማንኛውም ክፍት ቦታ፣ በውሀ አካላት፣ በአረንጓዴ ቦታዎች፣ የፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦዎች ውስጥ፣ አጥር ጥግ፣ የመንገድ አካፋዮች ወዘተ መጣል ወይም እንዲጣል ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

፪. ማንኛውም የጽዳት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት/ማህበር ኤጀንሲው ለደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃነት ከፈቀደው ቦታ ውጭ ደረቅ ቆሻሻን ማስቀመጥ፣መጣል፣ማቃጠል ወይም መቅበር የተከለከለ ነው፡፡

4. It is prohibited for anybody to collect, accumulate and transport solid wastes which could be used for reusing or recycling purpose found at landfills without having a legal permit from the agency.

5. Any organization that collects solid wastes which could be used for reusing or recycling purpose and utilize it should have a licence or testimonial from the agency.

## Part Three

## Solid Waste Disposal

### 9. Prohibited Actions

1. It is prohibited to dump or cause the dumping of any solid wastes on the street, rail road's, bus stations and stops, pedestrian sides, roundabouts, at any open space, water bodies, green areas, sewage lines, fence sides, median strips and so forth.

2. It is prohibited for any cleaning service providing organization or association to put, dump, burn or bury solid wastes in any place except those permitted for solid waste disposal by the agency.

፫. ማንኛውም የጽዳት አገልግሎት ሰጪ ማህበር ኤጀንሲው ለደረቅ ቆሻሻ ጊዚያዊ ማቆያ ከፈቀደው ቦታ ውጭ ማንኛውንም ዓይነት ደረቅ ቆሻሻ ማስቀመጥ ወይም ማከማቸት የተከለከለ ነው፡፡

፬. ማንኛውም አሽከርካሪ ሆነ ተሳፋሪ ከመኪና ውስጥ ሆኖ በመስኮትም ይሁን በበር በኩል ማንኛውንም ዓይነት ደረቅ ቆሻሻ መወርወር ወይም መጣል የተከለከለ ነው፡፡

፭. ከንግድ ድርጅት/መኖሪያ ቤት የመነጨ ደረቅ ቆሻሻን ጠርጎ ወደ መንገድ ዳር ማስቀመጥ ወይም መጣል የተከለከለ ነው፡፡

**፲. <u>የተጣሉ ግዴታዎች፡-</u>**

፩. ማንኛውም ሰው ከቤት ውጭ በእንቅስቃቀሴ ምክንያት የሚመነጩ ጥቃቅን ቆሻሻዎች (የሶፍትና የወረቀት ቁርጥራጮች፤ የተለያዩ የምግብ፤ የመጠጥና ትናንሽ እቃዎች ማሸጊያዎች፤ የማስቲካና የከረሜላ ልጣጭ ወዘተ) በመንገድ ዳር በተቀመጡ የጥቃቅን ቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች የማስቀመጥ ግዴታ አለበት፡፡

3. It is prohibited for any cleaning service providing association to put or accumulate any type of solid wastes in any place except the temporary stations for the thereof permitted by the agency.

4. It is prohibited to throw or dump any type of solid wastes for a driver or passengers by the window or opening the door while sitting in a car.

5. It is prohibited to put or dump solid wastes on the road side which are generated from sweeping a house or business organization.

**10. <u>Obligations</u>**

1. Any person shall have the obligation to put small solid wastes (soft papers and trash papers, various food and small drinks containers, covers of chewing gums and candies and so forth) generated outside of houses due to movement in dustbins placed at road sides.

፪. በንፋስ የሚበተን እቃ ጭኖ በመንገድ የሚንቀሳቀስ ማንኛውም የጭነት ተሽከርካሪ ሙሉ በሙሉና በአግባቡ ሸፍኖ የመንቀሳቀስ ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል አራት
## የጥቃቀን ደረቅ ቆሻሻ ማስቀመጫ ደስት ቢን አጠቃቀምና አያያዝ

### ፲፩. የተከለከሉ ድርጊቶች፡-

፩. በመንገድ ዳር በሚቀመጡ የጥቃቅን ደረቅ ቆሻሻ ማስቀመጫ እቃዎች ላይ ከቤት፣ ከድርጅትና ከገበያ ማዕከላት የመነጨ ደረቅ ቆሻሻ ማስቀመጥ የተከለከለ ነው፡፡

፪. የሞቱ እንስሳትን በመንገድ ዳር በሚቀመጡ የጥቃቅን ደረቅ ቆሻሻ ማስቀመጫ እቃዎች ላይ መጣል የተከለከለ ነው፡፡

፫. በመንገድ ዳር በሚቀመጡ የጥቃቅን ደረቅ ቆሻሻ ማስቀመጫ እቃዎች ላይ ማስታወቂያ መለጠፍ፣ ተደግፎ ንግድ ማከናዎን፣ በላያቸው ላይ እቃ ማስቀመጥና ማስደገፍ የተከለከለ ነው፡፡

፬. በመንገድ ዳር በሚቀመጡ የጥቃቅን ደረቅ ቆሻሻ ማስቀመጫዎች ላይ ከወረዳው ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽ/ቤት እውቅና ውጭ ከአካባቢው ማስወገድ፣ መንቀል፣ ቦታቸውን መቀየር፣ ለሌላ አገልግሎት ማዋል የተከለከለ ነው፡፡

2. Any truck shall have the obligation to fully and properly cover and move while carrying materials that could be dispersed due to wind.

## Part Four
## Utilization and Management of Dustbins Cans for Small Solid Wastes

### 11. Prohibited Actions

1. It is prohibited to dump solid wastes generated from houses, organizations and trade centers into dustbins which are placed at road sides.

2. It is prohibited to dump dead animals into dustbins which are placed at road sides.

3. It is prohibited to post advertisements, to lean and carry out business, put materials on and support the thereof on dustbins which are placed at road sides.

4. It is prohibited to remove, misplace, relocate dustbins placed at road sides from the area and use them for other purposes without the recognition of the woreda solid waste management office.

**፲፪. የተጣሉ ግዴታዎች**

፩. በመንገድ ዳር የሚቀመጡ የጥቃቅን ደረቅ ቆሻሻ ማስቀመጫዎች ኤጀንሲ በሚያወጣው የአሰራር ስታንዳርድ መሰረት የመንገድ ጽዳት ፈጻሚዎች (መንገድን እንዲያጸዱ የተፈቀደላቸው ድርጅቶች) ደስት ቢኑን የማጽዳትና ቆሻሻውን የማስወገድ ግዴታ አለባቸው፡፡

፪. ማንኛውም መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆነ ተቋም/ድርጅት ደንበኞቹ ወይም ጐብኝዎች ጥቃቅን ቆሻሻ የሚጥሉበት ማጠራቀሚያ ኤጀንሲው በሚያወጣው የጥቃቅን ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ስታንዳርድ መሠረት በበሩ ፊት ለፊትና በግቢው በውስጥ አመቺ በሆነ ሥፍራ ላይ በማስቀመጥ ደንበኞቹ እንዲጠቀሙ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

፫. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የአገልግሎት መስጫ ተቋምና የማምረቻ ድርጅት ለጥቃቅን ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ያስቀመጠውን ዕቃ በንፅህና የመጠበቅና በየጊዜውም የተጠራቀመውን ቆሻሻ በተገቢው ቦታ የማስወገድ ግዴታ አለበት

፬. ማንኛውም ድርጅት/ተቋም በአቅራቢያው በመንግስት ወይም በሌሎች ህጋዊ ፈቃድ ባላቸው አካለት የተቀመጡ የጥቃቅን ደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ደስት ቢኖችን ጉዳት እንዳይደርስባቸው በኃላፊነት የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡

**12. Obligations**

1. Those individuals that cleanse streets shall have the obligation to clean dustbins which are placed at road sides and remove their wastes as per the procedural standard set by the agency.
2. Any governmental and non-governmental institution/organization shall have the obligation to place dustbins in a suitable place at its entrance and inside the compound; and cause its customers or visitors to use the dustbins as per the standard set to collect small solid wastes by the agency.
3. Without prejudice to sub-article 2 of this article, any service rendering institution and manufacturing organization shall have the obligation to neatly maintain the dustbins they placed and properly dispose the collected waste at the appropriate place.
4. Any organization/institution shall have the obligation to responsibly watch over the dustbins not to be harmed which are placed at its vicinity by the government or other legally recognized organs.

## ክፍል አምስት

## የጽዳት አገልግሎት ሰጭ ማህበራት /ድርጅቶች የቆሻሻ አያያዝ

**፲፫. የተጣሉ ግዴታዎች፡-**

፩. ማንኛውም የጽዳት አገልግሎት ሰጭ ማህበር/ድርጅት የሰበሰበውን ደረቅ ቆሻሻ እስከሚጓጓዝ ድረስ ሸፍኖ የማስቀመጥ ግዴታ አለበት፡፡

፪. ማንኛውም የጽዳት አገልግሎት ሰጭ የጽዳት ማህበር/ድርጅት የሰበሰበውን ደረቅ ቆሻሻ ጽዳት ኤጀንሲው በሚያወጣው ስታንዳርድ መሰረት የማጓጓዝ ወይም እንዲጓጓዝ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

፫. ማንኛውም የጽዳት አገልግሎት ሰጭ ማህበር/ድርጅት መጥፎ ሽታ ሊፈጥሩ የሚችሉና ለጤና ስጋት የሆኑ ደረቅ ቆሻሻዎችን በልዩ ሁኔታ በፍጥነት ከአካባቢው ወደ ማስወገጃ ቦታ እንዲጓጓዙ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

፬. በህግ በተፈቀዱ ጊዜያዊ የደረቅ ቆሻሻ ማሰቀመጫ ቦታዎች የሚሰሩ የጽዳት ማህበራት/ድርጅቶች የማቆያ ቦታውን ከውስጥና ከግቢው ውጭ እሰከ 5 ሜትር ዙሪ ድረስ ጽዱና አረንጓዴ በማድረግ ቆሻሻው እንዳይበተን የማድረግ ግዴታ አለባቸው፡፡

## Part Five

## Waste Management of Cleaning Service Providing Associations/ Organizations

**13. Obligations**

1. Any cleaning service providing association/organization shall have the obligation to cover and place the solid waste it collected until the transportation of the thereof.

2. Any cleaning service providing sanitary association/organization shall have the obligation to transport or cause the transportation of the solid waste it collected as per the standard set by the sanitary agency.

3. Any cleaning service providing association/organization shall have the obligation to selectively and swiftly transport the solid wastes that could cause bad smell and affect ones health.

4. Sanitary associations/organizations that work at solid waste gathering place shall have the obligation to make the thereof clean and green inside and outside of its compound up to 5m radius so as to keep the scattering of wastes.

፭. ማንኛውም የጽዳት አገልግሎት ሰጭ ድርጅት የጽዳት ኤጀንሲ በሚያወጣው የአሰራር ስታንዳርድና መመሪያ መሰረት ለደንበኞች አገልግሎት መስጠት ይጠበቅበታል፡፡

5. Any cleaning service providing organization is expected to deliver service for customers as per the procedural standards and directives issued by the agency.

## ክፍል ስድስት
## ከተለያዩ ቦታዎች ስለሚመነጩ ደረቅ ቆሻሻዎች አያያዝና አወጋገድ

## Part Six
## Management and Disposal of Solid Wastes Generated from Various Places

### ፲፬. የተከለከሉ ድርጊቶች

፩. የሞቱ እንስሳትን በየትኛውም ቦታ መጣል የተከለከለ ነው፡፡

፪. ማንኛውም በከተማው የሚገኝ ስጋ ቤት የአጥንትና የስጋ ተረፈ ምርቱን ባልተፈቀደ ቦታ መጣል የተከለከለ ነው፡፡

፫. የተበላሹ የአትክልትና የፍራፍሬ ተረፈ ምርቶችን ከንግድ ማዕከሉ ግቢ ውጭ ወይንም መንገድ ዳር ማከማቸት፣ ማስቀመጥ ወይም መጣል የተከለከለ ነው፡፡

### 14. Prohibited Actions

1. It is prohibited to dump dead animals at any place.
2. It is prohibited for any butchery in the city to dump its leftovers in an unauthorized place.
3. It is prohibited to collect, place or dump rotten vegetables and fruits leftovers outside of the business center vicinity or at road sides.

### ፲፭. የተጣሉ ግዴታዎች፡-

፩. ማንኛውም የቤት እንስሳትን የሚያረባ ሰው/ድርጅት ከእንስሳቱ የሚወጡ እዳሪዎችንና የእንስሳቱ የምግብ ተረፈ ምርቶችን በአግባቡ የመያዝና በተፈቀደ ቦታ ብቻ የማስወገድ ግዴታ አለበት፡፡

### 15. Obligations

1. Any individual/organization that breeds cattle shall have the obligation to properly handle and dispose their dung and fodder leftovers in an authorized place only.

፪. የቤት እንስሳትን በመንገድ ይዞ የሚንቀሳቀስ ሰው/ድርጅት ከእንስሳቱ የሚወጡ እዳሪዎች በመንገድ ላይ ለሚፈጥሩት የጽዳት ችግር ኃላፊነት አለበት፡፡

፫. በከተማው በእንስሳት ጀርባ ተጭነው የሚጓጓዙ ሳር፣ ጭድና ቅጠላ ቅጠል አካባቢን በማያቆሽሽ መልኩ በአግባቡ ተሸፍኖ መሆን ይገባዋል፡፡

፬. በከተማው የሚገኙ ሕጋዊ ፈቃድ ያላቸው የእንስሳት የግብይት ማዕከላትን የሚያስተዳድሩ ድርጅቶች የገበያ ማዕከሉን ውስጥና የግቢውን ውጭ እስከ ፭ ሜትር ዙሪያ በቋሚነት በማጽዳት ቆሻሻውን በተፈቀደላቸው ቦታ ብቻ ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የማስወገድ ግዴታ አለባቸው፡፡

፭. በከተማው ለሰው ልጅ ጤንነት ችግር የሚፈጥሩ የቤት እንስሳትን የሚገድል ድርጅት/ተቋም እንስሳቱን ከመግደሉ በፊት ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት እቅዱን ለኤጀንሲው በማቅረብ ዝግጅት እንዲደረግ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

2. Any individual/organization that causes the movement of domestic animals on the street shall have the responsibility for the sanitary problem created on the road by the dung of the animals.

3. Grasses, hay and leafs which are transported by the back of animals should be properly covered not to mess the surrounding.

4. Organizations that administer recognized animals markets found in the city shall have the obligation to clean the inside and outside of the market center up to 5m radius permanently and dispose the waste only in an authorized place as per the directive to be issued by the agency.

5. Organization/ institutions that exterminate domestic animals, which are harmful to the health of individuals in the city, shall have the obligation to submit its plan as per the directive to be issued by the agency and cause the execution of preparations before exterminating the animals.

፮. የቤት እንስሳት የሞተበት ሰው/ድርጅት የሞቱ እንስሳትን አንስቶ ለሚያስወግዱ ድርጅት ወይም ለወረዳው ጽዳት ጽሕፈት ቤት በስልክ ወይም በአካል እንዲነሳለት የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

6. An individual/organization whose domestic animal is dead shall have the obligation to notify to organizations that remove dead animals or to the woreda sanitary office either by phone or in person and request for the disposal of the thereof.

፯. ማንኛውም የሞቱ የቤት እንስሳትን አንስቶ የሚያስወግዱ ድርጅት/የመንግስት ተቋም ጽዳት ኤጀንሲ በሚያወጣው ስታንዳርድ መሰረት ጤናንና አካባቢንና በማይጎዳ ሁኔታ የማስወገድ ግዴታ አለበት፡፡

7. An organization/ governmental institution that removes any domestic dead animals shall have the obligation to dispose the thereof in a way not to harm the health and environment as per the standard to be issued by the sanitary agency.

፰. በአትክልትና ፍራፍሬ ንግድ የተሰማራ ሰው/ድርጅት ተረፈ ምርቶቹን ለጤና ወይም ለአካባቢ ጎጂ ባልሆነ ሁኔታ በንግድ ማዕከሉ ግቢ ውስጥ በራሳቸው ወጭ ለዚሁ ተብሎ ባዘጋጁትና ክዳን ባለው ፍሳሽን ሊያስወጣ በማይችል ደረጃውን በጠበቀ ማጠራቀሚያ እቃ ውስጥ የማጠራቀም ግዴታ አለበት፡፡

8. An individual/organization involved in vegetable and fruits selling business shall have the obligation to collect the leftovers of such inside the premises of the trade center using a standardized container, having a lid and that do not pass liquid, prepared for such purpose by their own cost in a way not to harm the health or environment.

፱. ማንኛውም አትክልትና ፍራፍሬ የሚነግድ የገበያ ማዕከል ያመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የማስወገድ ግዴታ አለበት፡፡

9. Any trade center involved in vegetable and fruits selling business shall have the obligation to dispose the solid waste it generates as per the directive to be issued by the agency.

፲. ማንኛውም የአትክልትና የፍራፍሬ የሚነግድ ሰው/ድርጅት ከተሽከርካሪ ላይ አትክልትና ፍራፍሬ ሲጭንና ሲያወርድ የሚወዳድቁ ቆሻሻዎችን ወዲውኑ የማጽዳት ግዴታ አለበት፡፡

፲፩. ከግንባታ ቦታ ላይ በንፋስ በቀላሉ የሚበተን ወይም አካባቢን ሊያቆሽሽ የሚችል አሸዋ፣ ፍርስራሽ፣ ጠጠር፣ ጭቃ ጭኖ በመንገድ የሚንቀሳቀስ ማንኛውም የጭነት ተሽከርካሪ ሙሉ በሙሉ ከግንባታ ቦታው ሳይወጣ ሸፍኖ ወይም ጭቃውን አጥቦ የመንቀሳቀስ ግዴታ አለበት፡፡

፲፪. በግንባታ ወቅት ከግንባታ ማዕከሉ በተሽከርካሪው ጎማ አማካኝነትና ከጭነት መንጠባጠብ ምክንያት ከግንባታ ማዕከሉ ውጭ ለሚፈጠር የአፈር፣ የጭቃ፣ የአሸዋና የጠጠርና የፍርስራሽ መበተን አካባቢውን እንዳይቆሽሽ ግንባታው እስኪያልቅ ድረስ የግንባታው ባለቤት ቋሚ የጽዳት ባለሙያ ቀጥሮ አካባቢውን የማጽዳትና ንጹህ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

፲፫. ማንኛውም በከተማው የሚገኝ ስጋ ቤት የአጥንትና የስጋ ተረፈ ምርቱን በአግባቡ የመያዝ፣ መልሶ ጥቅም ላይ የማዋል ወይም የማስወገድ ግዴታ አለበት፡፡

10. Any individual/organization involved in vegetables and fruits selling business shall have the obligation to immediately clean scattered wastes during loading and unloading of the same.

11. Any truck loaded and move with sand, demolition, gravel and mud, which are easily spread by wind or make the environment dirty from construction sites shall have the obligation to cover such before leaving the site.

12. During construction, an owner of a construction shall have the obligation to hire a sanitation officer and clean the surrounding from wastes created outside of the construction site by the spread of soil, mud, sand, gravel and demolition due to truck tires and freight drops till the end of the construction.

13. Any butchery in the city shall have the obligation properly to handle, reuse and dispose the leftovers of bones and meat.

## ክፍል ሰባት
## የአደገኛ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ

### ፲፮. የተከለከሉ ድርጊቶች

፩. ማንኛውንም ዓይነት አደገኛ ደረቅ ቆሻሻ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ፈቃድ ሳያገኝ የማዘጋጃቤታዊ ደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ላይ ማስወገድ የተከለከለ ነው፡፡

፪. አደገኛ ደረቅ ቆሻሻ ከማዘጋጃቤታዊ ደረቅ ቆሻሻ ጋር ቀላቅሎ ማጓጓዝም ይሁን ማስወገድ የተከለከለ ነው፡፡

፫. ከጤና ተቋማት የሚመነጫ ደረቅ ቆሻሻን ከማዘጋጃ ቤታዊ ደረቅ ቆሻሻ ጋር ቀላቅሎ ማጠራቀም፣ ማጓጓዝ ወይም ማስወገድ የተከለከለ ነው፡፡

፬. የኤሌክትሮኒክስ ደረቅ ቆሻሻዎችን ሕጻናት በሚውሉባቸውና በሚጫወቱባቸው አካባቢዎች፣ በየመንገዱና በተገኙ ክፍት ቦታዎች መወርወርና እንዲወገዱ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

## Part Seven
## Management and Disposal of Hazardous Waste

### 16. Prohibited Actions

1. It is prohibited to dispose hazardous solid wastes at the landfills of municipal solid waste without having an authorization from the environmental protection authority of the Adds Ababa city government.
2. It is prohibited to transport and dispose hazardous solid wastes by mixing it with municipal solid wastes.
3. It is prohibited to collect, transport or dispose solid wastes generated from health facilities blended with that of municipal solid wastes.
4. It is prohibited to throw and cause the disposal of electronic solid wastes in places where children stay and play; and at the street and existing open spaces.

## ፲፯. የተጣሉ ግዴታዎች፡-

፩. አደገኛ ደረቅ ቆሻሻ የሚያመነጭ ሰው/ድርጅት ያመነጨውን አደገኛ ደረቅ ቆሻሻ ከማዘጋጃ ቤታዊ ደረቅ ቆሻሻ ለይቶ ማከማቸት ወይም ማስቀመጥ ግዴታ አለበት፡፡

፪. የኤሌክትሮኒክስ ደረቅ ቆሻሻዎች አያያዝና አወጋገድ ኤጀንሲ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የሰውንና የአካባቢን ጤንነትና ደህንነት በማይጎዳ ሁኔታ መወገድ ይገባዋል፡፡

፫. ማንኛውም ግለሰብ ወይም የከተማ ነዋሪ የደረቅ ቆሻሻን በሚያስወግድበት ወቅት ደረቅ ቆሻሻን በዓይነት መለየት የሚጠበቅበት ቢሆንም የኤሌክትሮኒክስ ቆሻሻዎችን በተለየ መልኩ በመለየት በደረቅ ቆሻሻን በመሰብሰብና በማስወገድ ሥራ ለተሰማሩ ሠራተኞች ማስረከብ አለበት፡፡

፬. በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ የተሰማሩ የጽዳት ሠራተኞች የኤሌክትሮኒክስ ቆሻሻዎችን በሚሰበስቡበትና በሚያጓጉዙበት ወቅት ከሌሎች የደረቅ ቆሻሻ ዓይነቶች ለይተው ለመልሶ መጠቀም በሚውልበት መልኩ መሆን አለበት፡፡

## 17. Obligations

1. An individual/organization that generates hazardous solid waste shall have obligation to separately accumulate or place the generated hazardous solid waste from the municipality solid waste.

2. Electronic solid wastes management and disposal should be carried out as per the directive to be issued by the agency in a way not to harm the health and wellbeing of individuals and the environment.
3. Any person or dweller of the city should particularly separate electronic solid wastes and deliver such to employees engaged in the collection and disposal of same even though it is expected to separate solid wastes as to their nature while disposing the thereof.

4. Sanitary workers engaged in the management and disposal of solid wastes should separate the thereof from other types of solid wastes while collecting and transporting same in a manner to use it for reuse.

፭. የኤሌክትሮኒክስ ቁሳቁስ አምራቾች፣ አስመጪ ድርጅቶች፣ ተጠቃሚ ድርጅቶችና ግለሰቦች ያረጁና አገልግሎት የማይሰጡ የኤሌክትሮኒክስ ቁሳቁሶችን በአግባቡና አካባቢን በማይበክል መንገድ እንዲወገዱ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

፮. ማንኛውም የጤና ተቋም በተቋሙ የሚመነጨውን የሜዲካል ደረቅ ቆሻሻ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ወይም የምግብና መድሃኒትና መጠጥ ቁጥጥር ባለስልጣን በሚያወጣው ስታንዳርድ መሰረት በሚገነባ ማቃጠያ ውስጥ ደረቅ ቆሻሻው እንዲቃጠልና እንዲወገድ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል ስምንት
## የተለያዩ አካባቢዎች ጽዳትና ቋሚ የጽዳት ቀን ስለመወሰን

### ፲፰. የተጣሉ ግዴታዎችና የተከለከለ ድርጊት

፩. ማንኛውም መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት፣ የንግድ ተቋም፣ ኢምባሲ፣ ከመስሪያ ቤቱ አጥር አጠገብ በ፭ ሜትር ክልል ውስጥ የሚገኘውን አካባቢ በቋሚነት ጽዱ የማድረግ፣ የመንከባከብና በአካባቢው ለተጣለ ደረቅ ቆሻሻ ኃላፊነት አለበት፡፡

5. Manufacturers, importers, organizational and individual consumers of electronic materials have the responsibility to cause the disposal of old and worn-out electronic materials properly and in a non-pollutant way to the environment.

6. Any health facility has the obligation to cause the burning and disposing of medical solid wastes it generates in an incinerator built as per the standard set by the environmental protection authority or food and pharmaceutical and drinks inspection authority.

## Part Eight
## Deciding Cleaning of Various Places and a Permanent Sanitary Day

### 18. Obligations and Prohibited Actions

1. Any government and non-governmental organization, business firm and embassy is responsible for the dumped solid wastes and to make clean and manage the vicinity within 5m radius of its office fence.

፪. ማንኛውም ነዋሪ ከመኖሪ ቤቱ አጥር አጠገብ በ፭ ሜትር ዙሪያ ክልል ውስጥ የሚገኘውን አካባቢ በቋሚነት ጽዱ የማድረግ፣ የመንከባከብና በአካባቢው ለተጣለ ደረቅ ቆሻሻ ኃላፊነት አለበት፡፡

፫. ወቅታዊና ልዩ ዝግጅቶች ማለት ፌስቲቫል፣ ባዛር፣ ኤግዚብሽን፣ የመንገድ ላይ ሩጫ፣ የተለያዩ ሰልፎች፣ ወዘተ የሚያዘጋጁ ድርጅቶች/ግለሰቦች የአካባቢውን ጽዳት ዝግጅቱ እስኪ ጠናቀቅ ድረስ በኃላፊነት የመጠበቅና የማጽዳት ግዴታ አለባቸው፡፡

፬. ዓመታዊ፣ ወርሃዊና ሳምንታዊ የእምነት በዓላት የሚያከናውኑ የእምነት ተቋማት ለምዕመኑ በአካባቢው ቆሻሻ እንዳይጣል የማስገንዘብና በዓሉ ሲጠናቀቅ በእለቱ አካባቢውን የማጽዳት ግዴታ አለባቸው፡፡

፭. የታክሲና ሚኒባስ ተራ አስከባሪዎች፣ የፓርኪንግ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች፣ በጫማ ጥገናና ጽዳት (ሊስትሮ) የተሰማሩ፣ በእረፍት ቀን (ቅዳሜና እሁድ) መንገድ ላይ እንዲነግዱ ህጋዊ ፈቃድ የተሰጣቸው ነጋዴዎች ወዘተ የሚሰሩበትን አካባቢ እስከ ፲ ሜትር ዙሪያ በቋሚነት የማጽዳት፣ የመንከባከብ ግዴታ አለባቸው፡፡

2. Any resident is responsible for the dumped solid wastes and to permanently make clean and manage the vicinity within 5m radius of its residence.

3. Organizations/individuals that host current and special events like festival, bazaar, exhibition, street run and various marches have the responsibility to keep the surrounding area tidy until such is over and clean it.

4. While carrying out annual, monthly and weekly rites, religious institutions have the obligation to aware its congregations not to dump solid wastes in the area and clean it on the same day after the rite is over.

5. Queue controllers of taxis and minibuses, parking service rendering organizations, shoe shiners and authorized weekend (Saturday and Sunday) marketers on the street shall have the obligation to permanently clean and manage their working area up to 10m radius.

፮. ማንኛውም በገበያ ማዕከል ውስጥ የሚነግድ ግለሰብ/ድርጅት ያመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ ኤጀንሲው በሚያወጣው የማጠራቀሚያ ስታንዳርድ መሰረት ያመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ በግቢው ውስጥ ማከማቸት ይገባዋል፡፡

፯. ማንኛውም በገበያ ማዕከል ውስጥ የሚነግድ ግለሰብ/ድርጅት ከሱቁ ወይም ከመደብሩ ፊት ለፊት የወደቁ ደረቅ ቆሻሻዎችን ወዲያውኑ የማንሳትና ንጹህ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

፰. አጠቃላይ በገበያ ማዕከሉ ጽዳት ለማስጠበቅ የገበያ ማዕከሉ አስተዳደሪ በራሱ ወጭ ቋሚ የጽዳት ባለሙያዎችን ቀጥሮ አካባቢውን በቋሚነት ማጸዳት ይጠበቅበታል፡፡

፱. ማንኛውም የገበያ ማእከል ያመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ ኤጀንሲው በሚያወጣው ስታንዳርድ መሰረት በዓይነት ለይቶ ማጠራቀም ይገባዋል፡፡

፲. ማንኛውም የገበያ ማእከል ያመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያና ስታንዳርድ መሰረት የማስወገድ ግዴታ አለበት፡፡

6. Any individual/organization that carries out business in a trade center should collect the solid waste it generates in its compound with a container, as per the standard set by the agency.

7. Any individual/organization that carries out business in a trade center shall have the responsibility to collect solid wastes in front of his/its shop or store and clean the area.

8. The administration of the trade center is expected to hire permanent sanitary employees in its own cost and clean the trade center regularly.

9. Any trade center should separate and collect the solid waste it generates as per the standard to be issued by the agency

10. Any trade center shall have the obligation to dispose the solid waste it generates as per the directive and standarde to be issued by the agency.

፲፩. የመንገድ ጽዳት አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች/ግለሰቦች መንገድ ግራና ቀኝ ጠርዞች፣ የእግረኛ መንገድና አካፋይ መንገድ ማጸዳት፣ ጥቃቅን ቆሻሻዎች የሚጣሉበት የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ዕቃዎችን ማራገፍ ግዴታ አለበት፡፡

፲፪. ማንኛውም በግል ድርጅት ወይም በማህበር ተደራጅቶ መንገድን የሚያፀዳ ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያና ስታንዳርድ መሰረት የመስራት ግዴታ አለበት፡፡

፲፫. በከተማው የሚንቀሳቀሱ የከተማ አውቶብሶችና ቀላል የከተማ ባቡሮች በትኬት ምክንያት ለሚፈጠር የአካባቢ የጽዳት ችግር ድርጅቶች ኃላፊነት አለባቸው፡፡

፲፬. የከተማ ባቡሩን የሚያስተዳድረው ድርጅት የባቡር ሀዲድ የተዘረጋባቸውን መስመሮችና የባቡር ፌርማታዎችን ሙሉ በሙሉ በቋሚነት ጽዳቱን የመጠበቅና የማጽደት ግዴታ አለበት፡፡

፲፭. በአዲስ አበባ ከተማ የወሩ የመጨረሻ አርብ ለትምህርት ቤቶችና ለመንግስትና ለግል መስሪያ ቤቶች እንዲሁም ቅዳሜ ለነዋሪውና በስራ ቦታቸው ላሉ ማንኛውም ተቋማት አጠቃላይ የጽዳት ቀን ይሆናል፡፡

11. Organizations/individuals involved in street cleaning service provision shall have the obligation to clean the left and right sides of a road, pedestrian sides and median strips as well as clear dustbins.

12. Any private organization/association involved in street cleaning service provision shall have the obligation to clean the street as per the directive and standarede to be issued by the agency.

13. The organizations that provide city bus and light rail system transportation service shall have the responsibility for the sanitary problems created on the environmentdue to their ticket.

14. The organization that administer all the railroad routes and train stops shall have the obligation to regularly manage and clean the thereof.

15. In Addis Ababa city, the last Friday and Saturday of the month shall be the sanitary day for schools and offices; and residents and any institution on their working place respectively.

፲፮. ሁሌም በወሩ የመጨረሻው ዓርብ ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ሁሉም የመንግስት መስሪ ቤቶች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የእምነት ተቋማት፣ ትምህርት ቤቶች፣ ኢምባሲዎች ውስጥ የሚገኙ ሰራተኞችና ኃላፊዎች በጋራ የስራ ቦታቸውን ግቢ እና ከግቢ ውጭ እስከ 5 ሜትር እንዲያፀዱ ይገደዳሉ፡፡

16. Employees and heads of governmental offices, non-governmental organizations, religious institutions, schools and embassies, as per the directive to be issued by the agency, shall have the obligation to clean their working place and 5m radius outside of it at every last Friday of a month.

፲፯. ሁሌም በወሩ የመጨረሻው ቅዳሜ ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ሁሉም የከተማው ነዋሪ የመኖሪያ አካባቢውን በጋራ ወጥቶ እንዲያጸዳ ይገደዳል፡፡

17. All residents of the city, as per the directive to be issued by the agency, shall have the obligation to clean their residential area together at every last Saturday of a month

፲፰. ክፍት ቦታዎችን የአካባቢው ነዋሪ በጋራ የማጽዳትና የመንከባከብ ግዴታ አለበት

18. Community residences shall have the obligation to clean and protect open spaces together

## ክፍል ዘጠኝ
## የደህንነት መጠበቂያ ስለመጠቀም፣ ግንዛቤ ስለመስጠት

### ፲፱. የተከለከሉ ድርጊቶች፡-

ማንኛውም የጽዳት አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅትና የኤጀንሲው ባለሙያ ኤጀንሲው በሚያወጣው ስታንዳርድ መሰረት ዩኒፎርምና የደህንነት መጠበቂያ ግብዓቶችን ሳይጠቀም አገልግሎት መስጠት የተከለከለ ነው፡፡

## Part Nine
## Using Safety Protection and Creating Awareness

### 19. Prohibited Actions

It is prohibited for any sanitary service rendering organization, agency workers to provide service without using uniform and safety protection materials as per the standard to be issued by the agency.

## ፳. <u>የተጣሉ ግዴታዎች፡-</u>

፩. ሁሉም የመንግሥትና የግል ትምህርት ተቋማት ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የአካባቢ ጥበቃና ጸዳት ክበብ የማቋቋም፣ ስለአካባቢ ጽዳት ለተማሪዎቹ ግንዛቤ የመፍጠርና የማስተማር እና ተማሪዎች የትምህርት ቤት አካባቢያቸውን እንዲያጸዱ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

፪. ለተለያዩ አገልግሎቶች በራሪ ወረቀቶችን የሚያሠራጭ ማንኛውም ድርጅት /ግለሰብ/ ተቋም በበራሪ ወረቀቱ ምክንያት ለሚከሰት የከተማ ጽዳት መጓደል ኃላፊነት አለበት፣

## <u>ክፍል አስር</u>
## <u>በደረቅ ቆሻሻ የጽዳት አገልግሎት ላይ ስለሚሰማሩ ደርጅቶች ግዴታዎች</u>

## ፳፩. <u>የተጣሉ ግዴታዎች፡-</u>

፩.. ማንኛውም የደረቅ ቆሻሻ የጽዳት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት በተሰጠው የመሥሪያ ክልል ውስጥ የተረከበውን የመስሪያ አካባቢ ለጤናና ለአካባቢ ችግር መንስኤ በማይሆን ሁኔታ ተገቢውን ጥንቃቄ በመውሰድ የመስራት ግዴታ አለበት፡፡

## 20. <u>Obligations</u>

1. All governmental and private schools shall have the obligation to form environmental protection and sanitary club, create awareness and educate about environmental sanitation for their students and cause them to clean the school environment as per the directive to be issued by the agency.

2. Any organization/individual/ institution that distribute fliers for various purposes shall have the responsibility for the sanitary problem created by the thereof.

## <u>Part Ten</u>
## <u>Obligations for Organizations Engaged in Solid Waste Cleaning Service</u>

## 21. <u>Obligations</u>

1. Any solid waste cleaning service rendering organization shall have the obligation to carry out its duty by taking proper care within the working place it received so as to not to cause harm to the health and environment.

፪. ከተለመደው የዕለት ተዕለት ስራዎች በተለየ ሁኔታ ከፍተኛ ቆሻሻ በሚመነጭባቸው የበዓልና የልዩ ዝግጅቶች ወቅት የጽዳት አገልግሎት ሰጭው ድርጅት በቂ ቅድመ ዝግጅት በማድረግ ፈጣን አገልግሎት የመስጠጥ ግዴታ አለበት፡፡

፫. ማንኛውም የደረቅ ቆሻሻ የጽዳት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ወይም የመልሶ መጠቀምና ኡደት ድርጅት ከደንበኛው ጋር ውል በገባው መሰረት የመስራት ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል አስራ አንድ
## የኤጀንሲውና የሌሎች ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት

### ፳፪. የኤጀንሲው ተግባርና ኃላፊነት፡-

በሌሎች ህጎች ለኤጀንሲው የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው ኤጀንሲው ለዚህ ደንብ አፈፃፀም ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

፩. በከተማው የደረቅ ቆሻሻ የጽዳት አገልግሎት ለመስጠት ለተሰማሩ ድርጅቶች የስራና የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

2. Aside from the daily routines, the cleaning service rendering organization shall have the obligation to make the necessary preparation and provide its service during holidays and various festivals where lots of wastes are being generated.

3. Any solid waste cleaning service rendering organization or reusing and recycling organization shall have the obligation to provide service to the customer in compliance with its contract

## Part Eleven
## Power and Duties of the Agency and Other Organs

### 22. Power and Duties of the Agency

Without prejudice to the power and duties bestowed to the agency by other laws, the agency shall have the following power and duties for the execution of this organization:

1. Provide job and competency assurance permit for organizations in the solid waste cleaning service provision in the city;

፪. በመንግስት ተሽከርካሪ የሚጓጓዘውን ደረቅ ቆሻሻ አዲስ መመሪያ በማዘጋጀት በጽዳት የሽርክና ማህበራት እንዲጓጓዝ ያደርጋል፡፡

፫. የጽዳት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶችን አገልግሎት አሰጣጥ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊውን ማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፡፡

፬. የጽዳት አገልግሎቱን ለማሻሻል እንዲቻል ልዩ ልዩ የማበረታቻና የቁጥጥር ስርዓት ይፈጥራል፡፡

፭. ይህንን ደንብ ለማስፈፀምና አገልግሎቱን ለማሻሻል አግባብ ካለው አካል ውክልና መስጠት ይችላል፡፡

፮. ማንኛውም የደረቅ ቆሻሻ የጽዳት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ኤጀንሲው በሚያዘጋጀው የቆሻሻ አያያዝ አሰባሰብና አወጋገድ ደንብና ደንቡን ለማስፈጸም የሚወጡ መመሪያዎችንና ስታንዳርዶችን ጥሶ ሲገኝ የተሰጠው ፈቃድ ይሠረዛል ወይም ከስራውም ያግዳል ::

፯. የከተማውን የመንገድ ጽዳት ለማዘመንና ለማሻሻል ኤጀንሲው የመንገድ ጽዳትን በሽርክና ለተደራጁ ማህበራት በውክልና ያሰራል፡፡

2. By preparing new directive Solid waste transported by government vehicles shall transport by cleansing share association.

3. Follow-up and control the service provision of sanitary service providing organizations as well as take the necessary corrective measure;

4. Create various motivational and controlling system in order to improve the sanitary service;

5. May delegate an appropriate organ so as to execute this regulation and improve the sanitary service;

6. The permit given to any solid waste cleaning service providing organization shall be revoked or suspended from acting if found violating the solid waste management, collection and disposal regulation and directives and standards issued for the implementation of the thereof by the agency.

7. To modernize and improve street cleansing of the city the agency can outsource street cleaning service to share holding association.

፰. የደረቅ ቆሻሻ አስተዳዳር ኤጀንሲ የመልሶ መጠቀምና ኡደት ድርጅቶችን ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፡፡ እንዲሁም የመልሶ መጠቀምና ኡደት ሊያዘምኑ የሚችሉ አሰራሮችን በጥናት ለይቶ ይተገብራል፡፡

8. Solid waste management agency shall control, follow-up and support reusing and recycling organizations, and identify methods that enhance the reusing and recycling procedures and implement same.

## ፳፫, የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽሕፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት፡-

በሌሎች ሕጎች የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽሕፈት ቤት በከተማው አስተዳደር ክልል የሚፈፀም የአካባቢ ጽዳት መጓደልን፣ ማንኛውንም ህገወጥ ቆሻሻ መጣልንና ዝውውርን፣ በመንገድ ዳር የተተከሉ የጥቃቅን ደረቅ ቆሻሻ ማስቀመጫ እቃዎችን ጉዳትና ስርቆትን ከፖሊስ ጋራ በመሆን፣ ይከላከላል፣ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፣ ወይም ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ሥልጣን ላለው አካል ያስተላልፋል፡፡

## 23. Power and Duties of the Office of the Code Enforcement Service

The office of the code enforcement service, without prejudice to the power and duties bestowed for it by other laws, prevents the harm done on environmental sanitary, any illegal waste dumping and transfer, damage and stealing of dustbins placed at roadsides, take lawful measures; or cause the taking of lawful measures by other organs.

## ፳፬. የክፍለ ከተማ ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት

**የክፍለ ከተማ ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት፡-**

፩. የክፍለ ከተማው ህብረተሰብ በቋሚነት አካባቢውን እንዲያፀዳ በንቅናቄው እንዲሳተፍ ያቅዳል፣ ይመራል፣ ያስተባብራል፡፡

## 24. Power and Duties of Sub-City solid waste management office

**The sub-city solid waste management agency:**

1. Plan, lead and coordinate the community of the sub-city to clean its environment regularly and participate in the mobilization process.

፪. በክፍለ ከተማው ለሚገኙ ወረዳዎች የጽዳት የስራ እቅድ ያቅዳል፣ ያከፋፍላል፣ ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ቆጣጠራል፡፡

፫. በክፍለ ከተማው የሚሰሩ የጽዳት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፣ ይመራል፡፡

፬. በክፍለ ከተማው ለሚከሰት የጽዳት መጓደል ኃላፊነት አለበት፡፡

**፳፭. <u>የወረዳ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት፡-</u>**

**የወረዳ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት፡-**

፩. የወረዳው ነዋሪዎች የአካባቢያቸውን ጽዳት እንዲጠብቁ ግንዛቤ ይፈጥራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣

፪. ህገ-ወጥ ደረቅ ቆሻሻ የሚጥሉትን፣ ከተማ የሚያቆሽሹትን፣ ንብረት የሚያበላሹና የሚሰርቁትን፣ አጠቃላይ ይህንን ደንብ የሚተላለፉትን ድርጅቶች/ግለሰቦች ይቆጣጠራል በደንቡ መሰረምት እዲቀጡ ያደርጋል፡፡

፫. በወረዳው የሚንቀሳቀሱ የደረቅ ቆሻሻ ጽዳት አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶችን ቆጣጠራል፣ ይደግፋል፡፡

2. Plan, distribute, lead, coordinate and control the sanitary work plan for the woredas found in the sub-city.

3. Control, follow-up and lead the sanitary service providing organizations engaged in the sub- city.

4. Take responsibility for the improper cleaning exhibited in the sub-city.

**25. <u>Power and Duties of Woreda solid waste management office</u>**

**<u>Woreda solid waste management office</u>**

1. Create awareness for residents of the woreda about keeping the environment clean; coordinate and control same;

2. Control organizations/individuals that dump unauthorized solid wastes, make the city unclean, damage and steal properties; in general, cause their punishment as per the regulation that violate this regulation;

3. Control and support the solid waste sanitary service providing organizations operating in the woreda;

፬. በወረዳው የሚገኙ ጊዚያዊ ደረቅ ቆሻሻ ማቆያ ቦታዎችን በስታንዳርዱ መሰረት አገልግሎት መስጠጣቸውን ይከታተላል፤ ችግር ሲኖር በደንቡና መመሪያው መሰረት ዕርምት ዕርምጃ ይወስዳል፡፡

፭. በወረዳው የሚኖረው ነዋሪ ደረቅ ቆሻሻ በአግባቡ ሳያዝረከርክ እንዲያዝ፤ በዓይነት እንዲለይ ይከታተላል፤ ግንዛቤ ፈጥራል፤ ይቆጣጠራል፡፡

፮. በወረዳው የሚገኙ ነዋሪዎች በስታንዳርዱ መሰረት የጽዳት አገልግሎት እንዲያገኙ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

፯. በወረዳው ለሚከናዎነውን መንገድ ጽዳት ይቆጣጠራል፤እንዲሁም በወረዳው ለሚከሰት የጽዳት ችግር ኃላፊት አለበት፡፡

፰. በስታንዳርዱ መሰረት አገልግሎቱን በአግባቡ የማይሰጡ የጽዳት ድርጅቶች በደንቡ መሰረት አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡

፱. በወረዳው ለሚገኙ የትምህርት ተቋማት ለትምህርት ቤት ማህበረሰብ እንዲሁም የተለያዩ የእምነት ተቋማት ለምዕመኑ ግንዛቤ እንዲፈጥሩ አካባቢያቸውን እንዲያጸዱ ይከታተላል፡፡

4. Control that whether the temporary solid waste gathering places found in the woreda are providing service as per the standard; take corrective measures according to the regulation and directive where there is a problem;

5. Follow-up, create awareness and control that the residents of the woreda are handling the solid waste properly and collect same separately;

6. Have the responsibility to provide sanitary service for residents of the woreda in accordance with the standard;

7. Control the street cleaning carried out in the woreda; as well as take the responsibility for the improper cleaning exhibited in the woreda;

8. Based on the regulation, take administrative measures on the sanitary organizations that do not properly provide the service as per the standard;

9. Follow-up that schools and the various religious institutions in the wereda are creating awareness and cleaning their environment for their school community and worshipers respectively.

## ፳፮. የሌሎች አካላት ስልጣንና ተግባር፡-

ለዚህ ደንብ አፈፃፀም ሌሎች የተጠቀሱ አካላት ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖራቸዋል፣

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ በሁሉም የመንግስትና የግል ትምህርት ቤቶች የአካባቢ ጥበቃና የጽዳት ክበብ እንዲቋቋምና ስለደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ግንዛቤ እንዲፈጠር የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

፪. የአውቶብስና የባቡር አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች በትኬት ምክንያት ለሚከሰት የጽዳት ችግር መፍተሄ የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው፡፡

፫. የተለያዩ የእምነት ተቋማት ለምዕመኑን ስለ አካባቢ ጽዳት ግንዛቤ መፍጠርና የእምነት ተቋሙን አካባቢ ጽዱና አረንጓዴ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

፬. ወቅታዊና ልዩ ዝግጅቶች ማለት ፌስቲቫል፣ ባዛር፣ ኤግዚቢሽን፣ የመንገድ ላይ ሩጫ፣ ልዩ በዓላት ለምሳሌ መስቀል፣ የጥምቀት አረፋና መውሊድ ፕሮግራሞች የሚያዘጋጁ አካላት ኃላፊነት ወስደው አካባቢውን የማጸዳትና ጽዳቱን የሚያስጠብቅ ኮሚቴ በተለየ መንገድ ከክፍለ ከተማው ጽዳት ጽ/ቤት ጋር በቅንጅት የማቋቋም ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## 26. Power and Duties of Other Organs

For the implementation of this regulation, other stated organs shall have the following indicated duties and responsibilities:

1. The Addis Ababa city government education bureau shall have the responsibility to cause the establishment of environmental protection and sanitary club in all governmental and private schools and provide education about an integrated solid waste management system by inculcating same in the formal education curriculum.
2. Organizations that provide bus and train service shall have the responsibility to change their paper ticketing system to electronic card.
3. The various religious institutions shall have the responsibility to create awareness about environmental sanitation to its worshipers and make the surrounding of the thereof clean and green.
4. Organs that prepare current and special events like festivals, bazaar, exhibitions, street run, and specific holidays such as the finding of the true cross (Meskel), Epiphany, Arafa and Mawlid shall take the responsibility to clean the area and establish a particular committee in collaboration with the sub-city's sanitary office which ensures the sanitation.

፭. የትራፊክ ፖሊስ በዚህ ደንብ ውስጥ ከተሽከርካሪ ጋር ተያይዞ ለሚደርሱ የጽዳት መጓደል የደንብ ጥሰትና በመንገድ ዳር የተቀመጡ የጥቃቅን የደረቅ ቆሻሻ ማስቀመጫ ግብዓቶች በመኪና ግጭት ሲደርስባቸው ተከታትሎ ይይዛል፤ ይቆጣጠራል፤ ለህግም ያቀርባል፤ ደንብን ለማስፈፀም ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች የመተባበርና ፈጣን ምላሽ የመስጠት ግዴታ አለባቸው፡፡

፮. በሌሊት ክፍለ ጊዜ ተረኛ ሆነው የሚሰማሩ መደበኛ ፖሊሶች ጨለማን ተገን አድርገው ባልተፈቀደ ቦታ በህገወጥ መንገድ ደረቅ ቆሻሻ የሚጥሉትንና ከተማ የሚያቆሽሹትን ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች የመቆጣጠርና ለህግ እዲቀርቡ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

፯. የተለያዩ የመንግስት ተቋማት ማለትም ትምህርት ቢሮ፤ ንግድ ቢሮ፣ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን፣ ውበት መናፈሻና ዘላቂ ማረፊያ፣ ጤና ቢሮ፣ ባህልና ቱሪዝም፣ የመገናኛ ብዙሃን፤ ፖሊስ፤ ደንብ ማስከበር፤ ውሀና ፍሳሽ ባለስልጣን፤ መንገዶች ባለስልጣን፤ ቤቶችና ኮንስትራክሽን፣ የከተማ ባቡርና አውቶብስ ድርጅት ወዘተ ለከተማዋ ጽዳት መሻሻል ከኤጀንሲው ጋር በቅንጅት መስራት አለባቸው፡፡

5. In this regulation, traffic policemen shall arrest, control and bring to justice those responsible bodies that damage dustbins placed at sidewalks, violate code and cause the improper cleaning related with vehicles; they have the obligation to cooperate and provide prompt response upon a request in order to execute this regulation.

6. The regular policemen working in the night shift shall have the responsibility to control and bring to justice those individuals or organizations that dump solid wastes unlawfully in an unauthorized place and make the city dirty by using the night as a shield/cover.

7. For the improvement of the city cleansing different government organization such as trade bureau, education bureau, environmental protection authority, beauty park and cementery, health bureau, communication media, police, code enforcement, water and sewerage authority, culture and tourism, road authority, housing and construction, city train and bus organization etc shall work in collaboration with agency

## ክፍል አስራ ሁለት

## ስለ አገልግሎት ክፍያና ማበረታቻ

### ፳፯. ስለጽዳት አገልግሎት ክፍያ፡-

፩. ማንኛውም ሰው ለሚያገኘው የጽዳት አገልግሎት አግባብ ባለው ህግ የተወሰነውን የጽዳት አገልግሎት ክፍያ የመፈፀም ግዴታ አለበት፡፡

፪. የጽዳት አገልግሎት ማስፈጸሚያ እንዲሆን ከማንኛውም ቆሻሻን ከሚያመነጨው ህብረተሰብ ክፍልም ሆነ ከአገልግሎት ሰጭ ወይም ከአምራች ድርጅቶች ገቢ የሚሰበሰብ ይሆናል፡፡

፫. አካባቢን በመበከል ከፍተኛ ተጽዕኖ ያላቸውን ምርቶችን የሚያመርቱ ፋብሪካዎች፤ የመጠጥና የምግብ አምራች ድርጅቶች፣ የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት (ቴሌ፣ የትራንስፖርት ሰጪ ድርጅቶች ወዘተ) እና የተለያዩ የንግዱ ማህበረሰብ ፣ በበከሉት ልክ እንዲከፍሉ በጥናት ላይ የተመሰረተ የፋይንስ ደንብ በማዘጋጀት በደረቅ ቆሻሻ አስተዳዳር ኤጀንሲ የባንክ አካውንት ገቢ በመሰብሰብ ለደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ፣ አጓጓዝና ፤ መልሶ መጠቀምና ኡደት፤ ማስወገድና ለአዳዲስ ቴክኖሎጂ ፈጠራና ማበረታቻ አገልግሎት እንዲውል ይደረጋል፡፡

## Part Twelve

## Incentives and Service Charges

### 27. Sanitation Service Charges

1. Any person shall have the obligation to pay sanitation service charges which is specified by the relevant law for the sanitary service being provided.

2. A contribution shall be collected from the income of any segment of the community, service rendering or manufacturing organization that generate wastes for the execution of sanitary service provision.

3. Factories, food and drink processing organization, service rendering institutions, (telecommunication, transport service rendering organizations) and trade communities, that produce highly environmental polute products, to pay as per of pollute based on a study and a financial status regulation shall be prepared for such purpose; and the collected income shall be deposited in the bank account of the solid waste management agency for the collection, transportation, reuse and recycling, new technology innovation and motivation and disposal service of solid wastes.

**፳፰. ስለማበረታቻ**

፩. በጽዳት አገልግሎትና በመልሶ መጠቀምና ኡደት ሥራ ላይ ለሚሠማሩ የግልና የጽዳት ህብረት ሽርክና ድርጅቶች አግባብ ባለው ሕግና የሚመለከተው አካል በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ለተወሰኑ ዓመታት የከተማው አስተዳደር ከሚሰበስባቸው የተለያዩ ታክሶች ምህረት ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡

፪. በጽዳት አገልግሎት የተሰማሩ ህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር ኤጀንሲው በሚያወጣው ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ መሠረት በመንግሥት ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች በቅናሽ ወይም በተመጣጣኝ ክፍያ አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋሉ፡፡

፫. በደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና መቀነስ ላይ ጉልህ አስተዋጽኦና ልዩ የፈጠራ ፕሮጀክቶች፣ ቴክኖሎጂዎች ወይም ልዩ ልዩ ተግባራትን ላከናወኑ ሰዎች ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የማበረታቻ ሽልማትና እውቅና ሊሰጣቸው ይችላል፡፡

**28. Incentives**

1. The City Administration may exempt private organizations and sanitary work share cooperatives that are engaged in the sanitary service and reusing and recycling activities from the various taxes it collects for some years in accordance with the directive to be issued by the concerned body and relevant law,

2. Unions or share sanitary associations engaged in sanitary service shall be allowed to get service from public landfills with a cheap or reasonable price according to the implementation detailed directive to be issued by the agency.

3. Incentives and recognition may be given to individuals who made vivid contributions and carry out peculiar creative projects, technologies or various activities on solid wastes reusing and reduction, as per the directive to be issued by the agency.

፬. ኤጀንሲው በተለይም በጽዳት አገልግሎት ሥራ ላይ የተሰማሩ የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት ሥራቸውን ለማስፋፋትና አገልግሎታቸውን ለማጠናከር የሚያስችል በረጅም ጊዜ የሚከፈል የገንዘብ ብድር እንዲያገኙ ከሚመለከታቸው የአበዳሪ ድርጅቶችና ተቋማት ጋራ በመነጋገር ሁኔታዎችን ሊያመቻች ይችላል፡፡

4. The agency may facilitate conditions for sanitary associations engaged in sanitary service provision to get loans from the concerned lender organizations and institutions which is to be paid in long term in order to expand their work and strengthen their service.

፭. የደረቅ ቆሻሻ አሰባሠብና ማጓጓዝ ሥራውን ለማገዝ ተደራጅተውና አስፈላጊውን ፎርማሊቲ አሟልተው ለተገኙ የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት አገልግሎት የሚሰጡ የጽዳት ተሽከርካሪዎች በረጅም ጊዜ ክፍያ እንዲሸጡላቸው ሁኔታዎች ይመቻቻሉ፡፡

5. Conditions shall be facilitated for sanitary service provision share cooperative enterprises that are organized to support the collection and transportation of solid wastes and fulfill the necessary formality, to get dump trucks for long term payment.

## ክፍል አስራ ሶስት
## ስለአስተዳደራዊ ቅጣትና እርምጃ

## Part Thirteen
## Administrative Penalty and Measure

### ፳፱. አስተዳደራዊ ቅጣትና እርምጃ፡-

አግባብ ባለው የወንጀል ህግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህንን ደንብ የጣሰ ማንኛውም ሰው የሚከተሉት አስተዳደራዊ ቅጣቶች ይዋሰኑበታል /እርምጃዎች ይወሰዱበታል፡-

፩. የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽሕፈት ቤት፡-

### 29. Administrative Penalty and Measure

Without prejudice to the provisions specified in the relevant criminal code, the following administrative penalties or measures shall be taken on any person that violates this regulation.

1. The code enforcement service office:

ሀ. በደንብ ማስከበር ደንብ መሠረት እንደጥፋቱ ሁኔታ ድርጊቱን የማስቆም፣ የማዘጋት፣ የማሸግ፣ የማስነሳት እርምጃ ይወስዳል፤

ለ. በደንብ ማስከበር ደንብ መሠረት አስተዳደራዊ ቅጣት ይቀጣል፤

፪. ማንኛውም የደረቅ ቆሻሻ የጽዳት አገልግሎት ሰጭ ድርጅት የቆሻሻ አያያዝ፣ አሰባሰብና አወጋገድ ደንብ፣ መመሪያና ስታንዳርድ ከጣሰ ፈቃዱ ይሠረዛል፣ ወይም ይታገዳል፡፡

፫. ቆሻሻ ባልተፈቀደ ቦታ የጣለ ማንኛውም ሰው/ድርጅት የሚቀጣው ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ ያለአግባብ የጣለውን ደረቅ ቆሻሻ በራሱ ወጭ አንስቶ በህጋዊ ማስወገጃ ቦታ እንዲያስወግድ ይደረጋል፡፡

**፴. ቅጣትን ስለማስፈፀም**

ቅጣቱ የሚፈፀመው በደንብ ማስከበር ደንብ በተደነገገው መሠረት ይሆናል፡፡

a. According to the code enforcement regulation, it shall take measures of prevention, closing, cessation and removing the action as per the nature of the offence.

b. According to the code enforcement regulation, it shall take administrative penalty.

2. The permit of any solid waste sanitary service providing organization shall be revoked or suspended where it violates the regulation, directive or standards of the management, collection and disposal of wastes.

3. Any person/organization that dumps a waste in an unauthorized place, without prejudice to the penalty it receives, shall be forced to remove the solid waste it improperly dumped and dispose it at a permitted landfill at its own cost.

**30. Penalty Execution**

The penalty shall be executed in accordance with the specified provisions under the code enforcement regulation.

### ፴፩. ስለአቤቱታ አቀራረብ፡-

የአቤቱታ አቀራረብና አወሳሰን በደንብ ማስከበር ደንብ በተደነገገው መሠረት ይፈፀማል፡፡

## ክፍል አስራ አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፴፪. የመተባበር ግዴታ

ማናቸውም ሰው ይህን ደንብ በማስፈፀም ረገድ በዚህ ደንብ ከተጠቀሱት አካላት ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

### ፴፫. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ይህን ደንብ በሚገባ ለማስፈፀም ኤጀንሲው መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

### ፴፬. ስለተሻሩና ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

፩. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቆሻሻ አያያዝ፣ አሰባሰብና አወጋገድ ደንብ ቁጥር ፲፫/፲፱፻፺፮ ተሽሮ በዚህ ደንብ ተተክቷል፡፡

### 31. Appeal Submittal

Appeal submittal and decision making shall be carried out according to the promulgation of the thereof under the code enforcement regulation.

## Part Fourteen
## Miscellaneous Provisions

### 32. Duty to Cooperate

Any individual shall be bound to cooperate with the indicated organs in this regulation for the implementation of the thereof.

### 33. Power to Issue Directives

The agency may issue directives for the effective implementation of this regulation

### 34. Repealed and Inapplicable Laws

1. The Addis Ababa city government waste management, collection and disposal regulation number 13/2004 is repealed and substituted by this regulation.

፪. ማንኛውም የአስተዳደሩ ደንብ፣ መመሪያ፣ የተለመደ አሠራር ወይም ሥነ-ሥርዓት የተፃፈም ቢሆን ሣይፃፍ በልማድ የሚሠራበት ሁሉ ይህን ደንብ የሚቃረን ከሆነ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

፴፭. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከግንቦት ፳፭ ቀን ፪ሺ፲ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት ፳፭ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም**

**ድሪባ ኩማ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

2. Any regulation, directive, customary practice or procedure of the government and all written or non-written procedures, which are inconsistent with this regulation, shall not be applicable on matters covered under this regulation.

**35. <u>Effective Date</u>**

This regulation shall enter into force as of the 2nd day of June,2018.

**Done at Addis Ababa, this 2nd day of June,2018**

**Diriba Kuma**

**Mayor of the Addis Ababa City**